# የካምፓስ ወላጅ (Campus Parent) መመሪያ

ይህ የእርስዎ Campus Parent መነሻ ገጽ ነው። ለማሰስ በግራ በኩል ያሉትን ትሮች ይጠቀሙ። ቅንብሮችን ለመለወጥ **የተጠቃሚ ምናሌ** አዶን ጠቅ ያድርጉ።




1. **የመልእክት ማዕከል** የዲስትሪክት እና የትምህርት ቤት ማስታወቂያዎችን ያሳያል። በገቢ መልዕክት ሳጥኑ ስር በመምህራን የተላኩልዎትን መልዕክቶች ማየት ይችላሉ።
2. **ዛሬ** ለተመረጠው ተማሪ ዛሬ ወይም ነገ የሚገቡ ማናቸውንም የትምህርት ስራዎች ያሳያል።
3. **ካለንደር** ለተመረጠው ተማሪ የትምህርት ስራዎች እና የአቴንዳንስ ክስተቶችን (እንደ መቅረት ወይም መዘግየት ያሉትን) ያሳያል። የትምህርት ስራዎች እና የአቴንዳንስ ክስተቶች ተጨማሪ ዝርዝሮችን ለመግለጥ ጠቅ ሊደረጉ የሚችሉ ሲሆን ቀኑን በማስተካከል ያለፉ እና የወደፊት ክስተቶችን ማየት ይችላሉ።
4. **የትምህርት ስራዎች** ለተመረጠው ተማሪ በቀን የተደረደሩ ሁሉንም የተጠናቀቁ የትምህርት ስራዎችን ከነጥቦች፣ ማስጠንቀቂያዎች እና የመምህራን ማስታወሻዎች ጋር ያሳያል። እንዲሁም ያመለጡ የትምህርት ስራዎችን ማጣራት ይችላሉ።
5. **ውጤቶች** የተማሪውን GPAን፣ ማንናቸውም የተለጠፉ ደረጃዎችን (እንደ የ ሴሚስተር አጋማሽያሉ) እና ለሁሉም ክፍሎች ወቅታዊ በሂደት ላይ ያለ ውጤትን ያሳያል። የትምህርት ስራዎች የውጤቶች ዝርዝርን ለማየት ውጤት የሚለውን ጠቅ ያድርጉ እና ተዛማጅ የትምህርት ስራዎች እና ውጤቶቻቸውን (ካለ) ለማየት ምድብ የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።
6. **የክፍል መጽሃፍ ዝማኔዎች** ባለፉት 14 ቀናት ውስጥ ያስመዘገቡትን ወይም በሌላ መንገድ የዘመኑትን ሁሉንም የትምህርት ስራዎች ይዘረዝራል።
7. **አቴንዳንስ** ለተመረጠው ጊዜ ለተመረጠው ተማሪ ሁሉንም የአቴንዳንስ ክስተቶችን (ቀሪዎችን እና ማርፈዶችን) ይዘረዝራል። በጊዜያት መካከል በመቀያየር የያለፈ ግዜመረጃዎችን ማየት ይችላሉ።
8. **የጊዜ ሰሌዳ** የተማሪ ቀን ፈረቃዎችን ጨምሮ ለእያንዳንዱ ጊዜ የተማሪ የጊዜ ሰሌዳን ያሳያል። የጊዜ ሰሌዳዎች ዓመቱን በሙሉ፣ ለሁሉም ጊዜያት እና ለሁሉም የተማሪ ምዝገባዎች ይታያሉ።
9. **አካዳሚያዊ ዕቅድ** ተማሪው አሁን ላይ ለመመረቅ የሚያስችለውን ዝቅተኛ ተፈላጊ ክሬዲቶችን ለማምጣት እያሳየ ያለውን ዕድገትያሳያል *(የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ብቻ)*
10. **ክፍያዎች** በአሁኑ ጊዜ ለእያንዳንዱ ተማሪ የዕዳ ክፍያዎችን የሚያሳይ ሲሆን በክሬዲት ካርድ፣ በዴቢት ካርድ ወይም በኤሌክትሮኒክ ቼክ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ ያስችልዎታል።
11. **ሰነዶች** ወላጆች የተማሪ ሪፖርት ካርዶችን እንዲመለከቱ እና እንዲያትሙ ያስችላቸዋል።
12. የ **ተጨማሪ** ትር ሁሉንም ሌሎች ብዙ የሚገኙ ፖርታል መሳሪያዎችን ያሳያል *(ለተጨማሪ ማብራሪያ ገጽ 2ን ይመልከቱ)*

ይህንን ምናሌ በግራ በኩል ካላዩ፣ በላይኛው ግራ ጥግ ላይ ያሉትን ሶስት መስመሮች ጠቅ ያድርጉ።

## በርካታ ተማሪዎች

በ Campus Parent ውስጥ ትር ወይም መሣሪያ ሲመርጡ፣ በነባሪነት የአንድ ተማሪ መረጃን ያሳያል። የተማሪው ስም እና ፎቶ ከላይ በቀኝ በኩል ይታያል። የሌላውን ተማሪ መረጃ ለማየት ለመቀየር፣ በቀላሉ ምስሉን/ስሙን ጠቅ ያድርጉ እና ከተቆልቋዩ ውስጥ ይምረጡ።

አንድን ተማሪ ከመረጡት በኋላ፣ Campus Parent ሌላ እስኪመርጡ ድረስ በነባሪነት የዛን ተማሪ መረጃ ያሳያል።



# More

| | |
|---|---|
| Address Information | የቤተሰቡን ስልክ ቁጥር እና አድራሻ ይመልከቱ |
| Assessments | ለግዛት፣ ለብሔራዊ እና ለዲስትሪክት ፈተናዎች የተማሪ ውጤቶችን ይመልከቱ። |
| Demographics | የተማሪ መረጃ እና ቤተሰባዊ ዝምድናዎች (የድንገተኛ ጊዜ ተጠሪዎች) |
| Family Information | የእውቂያ መረጃ እና የዝምድና መረጃ ለሁሉም የቤተሰብ አባላት |
| Important Dates | የዲስትሪክት በዓላት |
| Transportation | የአውቶቡስ እና/ወይም የመኪና ማቆሚያ ፈቃድ መረጃ። |
| Parent Access | የተማሪ የስኩሎጂ ኮርሶች እና የ FirstView መዳረሻ ኮድ |
| Online Verification and Residency | አዲስ ተማሪ ይመዝገቡ ወይም ዓመታዊ የማረጋገጫ እና የነዋሪነት ቅጽዎን ይሙሉ (ሲኖር) |

## እኔ እንዴት...

### የተማሪዬን ውጤት እመለከታለሁ?

*ብዙ ተማሪዎች ካሉዎት፣ መረጃዎቻቸውን ለማየት በላይኛው ቀኝ በኩል ተማሪ መምረጥ ይኖርብዎታል።*

የ**ውጤቶች** ትርን ጠቅ ያድርጉ። ለእያንዳንዱ ክፍል በሂደት ላይ ያሉ እና የተለጠፉ ውጤቶችን ያያሉ፣ እንዲሁም የበለጠ ዝርዝር የትምህርት ስራዎች ውጤቶችን እና መረጃዎችን ለማየት ክፍል በሚለው ላይ ጠቅ ማድረግ ይችላሉ። ለተጨማሪ መረጃ ገጽ 6ን ይመልከቱ።

### የሪፖርት ካርድ ያትሙ?

*ብዙ ተማሪዎች ካሉዎት፣ መረጃዎቻቸውን ለማየት በላይኛው ቀኝ በኩል ተማሪ መምረጥ ይኖርብዎታል።*

**ሰነዶች** የሚለውን ትር ይምረጡ እና ካርድ ሊያትሙለት የሚፈልጉበትን ሴሚስቴር ይምረጡ። ለተጨማሪ መረጃ ገጽ 6ን ይመልከቱ።

## የአቴንዳንስ መረጃን ይመልከቱ?

*ብዙ ተማሪዎች ካሉዎት፣ መረጃዎቻቸውን ለማየት ከላይ በኩል ተማሪ መምረጥ ይኖርብዎታል።*

**አቴንዳንስ** የሚለውን ትር ይምረጡ። የአሁኑ ሴሚስቴር ላይ ያሉ ሁሉም ቀሪዎች እና መዘግየቶች ይታያሉ። የበለጠ ዝርዝር ለማየት ኮርስ የሚለውን ጠቅ ያድርጉ ወይም በሴሚስቴሮች መካከል በመቀያየር ለማየት ከላይ ያሉትን ቀስቶች ይጠቀሙ። ለተጨማሪ መረጃዎች ገጽ 7ን ይመልከቱ።

## ክፍያዎቼን ልመልከት እና ልክፈል?

*ብዙ ተማሪዎች ካሉዎት፣ ሁሉንም ክፍያዎቻቸውን በአንድ ላይ ማየት ይችላሉ ወይም የግለሰብ ክፍያዎችን ለማየት አንድን ተማሪ ይምረጡ።*

ሁሉንም የተገመገሙ ክፍያዎችን ለማየት **ክፍያዎች** የሚለውን ትር ይምረጡ። እባክዎን በዚህ ጊዜ ሁሉም የትምህርት ቤት ክፍያዎች በ ኦንላይን ሊከፈሉ እንዳማይችሉ ልብ ይበሉ። ክፍያዎችን ሙሉ ወይም ከፋፍለው መክፈል ይችላሉ። ክፍያ ለመክፈል፣ **ወደ ጋሪ አክል** የሚለውን ጠቅ ያድርጉ፣ ከዚያም ክፍያዎን ለመገምገም እና ለመፈጸም **የእኔ ጋሪ** የሚለውም ጠቅ ያድርጉ። ለተጨማሪ መረጃ ገጽ 8ን ይመልከቱ።

## የእውቂያ መረጃዬን አዘምን?

ዝመናዎች በ **ተጨማሪ** ትር ስር ሊደረጉ ይችላሉ። እባክዎን ያስታውሱ በኦንላይን ማረጋገጫ እና በነዋሪነት መስኮት (በተለምዶ ከሚያዝያ-ሓምሌ) ወቅት ማንኛውም ዝማኔዎች በማረጋገጫ ማመልከቻ ውስጥ መካተት ስላለባቸው በመረጃ ላይ ለውጦችን ማድረግ አይችሉም። ለውጦች በ Campus Parent ውስጥ ከመታየታቸው በፊት በትምህርት ቤት ጽ/ቤት ሠራተኞች መገምገም እና መጽደቅ አለባቸው።

**ዋናውን የቤተሰብ ቁጥር ለማዘመን፣ የአድራሻ መረጃ የሚለውን ይምረጡ።** ሁሉንም የቤተሰብዎን አባላት አሁናዊዉንየመጀመሪያ ስልክ ቁጥር እና አድራሻ ያያሉ። በስልክ ቁጥሩ ላይ ለውጥ ለማድረግ ለመጠየቅ አዘምን የሚለውን ጠቅ ያድርጉ። አድራሻዎች በፖርታሉ ላይ ሊቀየሩ አይችሉም።

**የቤተሰብ ተጠሪ መረጃን ለማዘመን፣ የቤተሰብ መረጃ** የሚለውን ይምረጡ። የዚያን ግለሰብ ስልክ ቁጥር ወይም የኢሜይል አድራሻ ዝማኔ ለመጠየቅ በማንኛውም ስም ስር ዝማኔዎችን ጠቅ ያድርጉ።

**የድንገተኛ ጊዜ ተጠሪ መረጃን ለማዘመን፣ ስነ ሕዝብ** የሚለውን ይምረጡ እና ከላይ በቀኝ በኩል አንድን ተማሪ ይምረጡ (ብዙ ካሉዎት)። የድንገተኛ ጊዜ ተጠሪዎችን ማዘመን፣ ማከል ወይም ማንሳት ይችላሉ።

## የተማሪዬን ወቅታዊ የትምህርት ስራዎች ልመልከት?

*ብዙ ተማሪዎች ካሉዎት፣ የግለሰብ አሳይመንቶቻቸውን ለማየት ከላይ በቀኝ በኩል አንድን ተማሪ ይምረጡ።*

ከሁሉም ክፍሎች የሚመጡትን የትምህርት ስራዎች ለማየት **የትምህርት ስራዎች** ላይ ጠቅ ያድርጉ። እባክዎን እነዚህ ከመጀመሪያው እስከ የቅርብ ጊዜ የተደራጁ መሆናቸውን ልብ ይበሉ፣ ከታች ያሉት በጣም የቅርብ ጊዜ የትምህርት ስራዎች ናቸው። ጊዜ ያለፈባቸው የትምህርት ስራዎች በቀይ ይታያሉ - ሁሉንም ጊዜ ያለፈባቸውን አሳይመንቶች ለማየት **ያመለጡ** የሚለው ላይ ጠቅ ማድረግ ይችላሉ።




## የ Parent Portal የይለፍ ቃሌን ቀይር?

ከላይ በቀኝ በኩል ያለውን የተጠቃሚ ምናሌ አዶን ጠቅ ያድርጉ እና **የመለያ ቅንብሮችን** ይምረጡ። በ**ይለፍ ቃል** ስር **ዝማኔ** የሚለውን ጠቅ ያድርጉ። ጠንካራ የይለፍ ቃል ማስገባት አለብዎት፣ ካልሆነ ስርዓቱ አይቀበለውም። የይለፍ ቃል መስፈርቶችን ለማየት ጠቋሚ ቀስትዎን የይለፍ ቃል ጥንካሬ ሳጥን ላይ ያንዣብቡ።

## የመለያ ደህንነት ኢሜይሌን ልመልከት/ላዘምን?

የመለያዎ የደህንነት ኢሜይል የተጠቃሚ ስምዎን ወይም የይለፍ ቃልዎን ከረሱ ጥቅም ላይ የሚውለው ኢሜይል ነው ። መለያዎን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲፈጥሩ የተዘጋጀ ነው እናም ከእውቂያ ኢሜይልዎ ጋር ሊለያይ ይችላል። ከላይ በቀኝ በኩል ያለውን የተጠቃሚ ምናሌ አዶን ጠቅ ያድርጉ እና **የመለያ ቅንብሮች**ን ይምረጡ። በ**መለያ ደህንነት ኢሜይል** ስር የአሁኑ የደህንነት ኢሜልዎ ምን እንደሆነ ማየት ይችላሉ። መቀየር ከፈለጉ **ዝማኔ** የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።



# ውጤቶች

ውጤቶቻቸውን ለማየት **ውጤቶች** የሚለውን ይምረጡ እና አንድን ተማሪ ይምረጡ (የሚመለከተው ከሆነ)። **የአንደኛ ደረጃ ውጤቶች በፖርታሉ ላይ አይገኙም**፣ ነገር ግን ከ**ሰነዶች** አካባቢ ውስጥ የአንደኛ ደረጃ የሪፖርት ካርድ ማተም ይችላሉ።

በሴሚስተሩ ያሉትን ሁሉንም ክፍሎች በተማሪው የጊዜ ሰሌዳ ላይ ያያሉ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዓመት በሁለት ሴሚስተሮች (S1፣ S2) የተከፈለ ሲሆን መካከለኛ ትምህርት ቤት በ 4 ሩብ ሴሚተሮች (Q1፣ Q2፣ Q3፣ Q4) ይከፈላል።  ከላይ ያሉትን ቀስቶች በመጠቀም በሴሚስቴሮች መካከል መቀያየር ይችላሉ።




### የትምህርት ስራዎች ውጤቶችን ይመልከቱ

ለትምህርቱ የትምህርት ስራዎች መረጃ የሚገኝ ከሆነ፣ ከክፍሉ አጠገብ የደበዘዘ ግራጫ ቀስት ይኖራል። የትምህርት ስራዎች ምድቦችን ለማየት ጠቅ ያድርጉት።

የትምህርት ስራዎች በመምህራን በተገለጹ ምድቦች የተከፋፈሉ ሲሆኑ በእያንዳንዱ ምድብ የተገኘውን ጠቅላላ ውጤት ማየት ይችላሉ። **የግለሰብ አሳይመንቶችን እና ውጤቶችን ለማየት የመደመር አዶውን ጠቅ ያድርጉ።**




### ክብደቶች

መምህራን የሚሰጧቸውን የትምህርት ስራዎች በምድቦች ሊለያዩ እና ለእነዚህ ምድቦች የተለያዩ ክብደቶችን ሊሰጡ ይችላሉ።

አንድ ምድብ ከሌላው ከፍ ያለ ክብደት ከተሰጠው፣ በከፍተኛው ምድብ ውስጥ ያሉት የትምህርት ስራዎች ውጤቶች በጠቅላላ ውጤቶች ስሌት ውስጥ የበለጠ ይቆጠራሉ።

## ያመለጡ የትምህርት ስራዎች (ሁለተኛ ደረጃ ብቻ)

ያመለጡ የትምህርት ስራዎችንን ለማግኘት **የትምህርት ስራዎች** ላይ ጠቅ ያድርጉ




ይህ አካባቢ የድሮ እና የወደፊት ሥራዎችን ጨምሮ ከሁሉም ክፍሎች የተውጣጡ ሁሉንም የትምህርት ስራዎችን በቀን ይዘረዝራል።

1. በዝርዝሩ ውስጥ 'ያመለጡ' የትምህርት ስራዎችን ብቻ ለማጣራት ከላይ ያለውን '**ያመለጡ**' የሚለውን መቀየሪያ ጠቅ ያድርጉ።
2. <u>የቆዩ</u> ወይም <u>የወደፊት</u> ሴሚስቴር የትምህርት ስራዎችን ለማጣራት ከላይ ያለውን **'የአሁኑ ጊዜ'** መቀያየሪያን ጠቅ ያድርጉ።

## ሪፖርት ካርዶች

የሪፖርት ካርድ ለማተም **ሰነዶች** የሚለውን ትር ይምረጡ።  ለተለያዩ ሴሚስቴሮች በርካታ አማራጮችን ማየት ይችላሉ፣ ግን የትኛውንም ንጥል ቢመርጡ፣ **ምንጊዜም የቅርብ ሴሚስቴር የሪፖርት ካርድን ያትማል**።




አንዴ ምርጫ ካደረጉ፣ የሪፖርት ካርዱ እንደ pdf ሰነድ ይወጣል። በአሳሽዎ ቅንብሮች ላይ በመመርኮዝ በአሳሽዎ ውስጥ ብቅ ሊል ወይም ወደ ሙሣሪያዎ ማውረድ ይችላል።

ይህንን ሰነድ በመሣሪያዎ ላይ ማስቀመጥ ወይም በቀጥታ ማተም ይችላሉ።

# አቴንዳንስ

አቴንዳንስ በመምህራን አቴንዳንስ አወሳሰድ ላይ በመመርኮዝ በፖርታሉ ውስጥ በእውነተኛ ጊዜ ይዘምናል። ይሁን እንጂ፣ አቴንዳንስ በአቴንዳንስ ጸሐፊ ሂደት ውስጥ እስኪያልፍ ድረስ እንደ ተጠናቀቀ ተደርጎ አይቆጠርም። ይህ ማለት አንድ ተማሪ አስተማሪው ቀሪ ካደረገው በኋላ ዘግይቶ ከደረሰ፣ የአቴንዳንስ ፀሐፊው በቀኑ መጨረሻ ላይ አቴንዳንሳቸውን በሂደት ውስጥ እንዲያልፍ እስኪያደርግ ድረስ ፖርታሉ እንደቀሪ ሊያሳይ ይችላል።

በሴሚስቴሩ ውስጥ ለተማሪው ሁሉም መቅረቶች እና መዘግየቶች ጠቅላላ ቆጠራ ለማግኘት **የአቴንዳንስ** ትሩን ይምረጡ ከላይ ያሉትን ቀስቶች በመጠቀም ያለፉ ሴሚስቴሮችን ማየት ይችላሉ። የተዘረዘሩትን የአቴንዳንስ ክስተቶችን ዝርዝር ለማየት ግራጫውን ቀስት በክፍል ላይ ጠቅ ያድርጉ።




እንዲሁም **በካለንደር** ትር ውስጥ አቴንዳንስን ማረጋገጥም ይችላሉ። በካለንደር አናት ላይ ያለውን **የአቴንዳንስ** ቁልፍን ጠቅ ያድርጉ እና በተመረጠው ወር ውስጥ ሁሉም ቀናት ለተማሪው የአቴንዳንስ ክስተት ጥቁር ነጥብ ያሳያል። የአቴንዳንስ መረጃን ለማየት ቀን ይምረጡ።



# ክፍያዎችን መክፈል

የዲስትሪክት ተማሪዎች እና ወላጆች አሁን በኢ-ቼክ ወይም ቪዛ፣ ማስተርካርድ ወይም በ Discover ካርዶች በ Infinite Campus Parent Portal በኩል ኦንላይን አንዳንድ ክፍያዎችን መክፈል ይችላሉ።

ሁሉንም የተመደቡ ክፍያዎች ለማየት **ክፍያዎች** የሚለውን ትር ይምረጡ። ክፍያዎችን ለመክፈል፣ መክፈል ከሚፈልጉት ክፍያ(ዎች) ቀጥሎ **ወደ ጋሪ አክል** የሚለውን ጠቅ ያድርጉ እና **የእኔ ጋሪ**ን ጠቅ ያድርጉ። ለአንድ ተማሪ ክፍያዎችን ለማየት፣ ከ**ግለሰብ** ተቆልቋይ ውስጥ ይምረጡ።







**የእኔ ጋሪ**

ጋሪዎ የመረጡትን ሁሉንም ክፍያዎች ያሳያል።

ከፊል ክፍያ ለመፈጸም፡-

ከክፍያው ቀጥሎ ያለውን **የገንዘብ መጠን** ሳጥን ላይ ጠቅ ያድርጉ እና ለዚያ ክፍያ መክፈል የሚፈልጉትን መጠን ያስገቡ። ክፍያዎችን እስከ $5ዝቅ አድርገው መክፈል ይችላሉ፣ ግን ክፍያዎች በመክፈያው ቀን ሙሉ በሙሉ መከፈል አለባቸው።

የክፍያ ዘዴዎች፡-

የተዘረዘረ **የክፍያ ዘዴ** ከሌለ፣ ወይም የተዘረዘረው ዘዴ እንዲቀይር ከፈለጉ፣ **የክፍያ ዘዴን አክል** የሚለውን ጠቅ ማድረግ እና የክፍያ ዝርዝሮችዎን ማስገባት አለብዎት።

ክፍያ ማስገባት፡-

ጠቅላላውን መጠን በተዘረዘረው የመክፈያ ዘዴ ለመክፈል፣ **ክፍያ አስገባ** የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።

# የክፍያ ዘዴዎች

ከዚህ በፊት ያስገቧቸው ማንኛውም አሁናዊ የክፍያ ዘዴዎች እዚህ ይታያሉ። የክፍያ ዘዴ ዝርዝሮችን ለመገምገም ወይም ለማርትዕ፣ ቀጥሎ ያለውን ግራጫ ቀስት ጠቅ ያድርጉ።

አዲስ የክፍያ ዘዴ ለማስገባት**አዲስ** የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።




ቼክ፣ ቁጠባ፣ ወይም ክሬዲት/ዴቢት ካርድ ይምረጡ፣ ከዚያም የመለያ ዝርዝሮች ወይም ካርድ ቁጥር ያስገቡ።

**ቅጽል ስም** የተለያዩ የመክፈያ ዘዴዎችዎን መለየት እንዲችሉ ለእርስዎ ብቻ የታሰበ ነው።

**ለቼክ/ቁጠባ ሂሳቦች፣ በአካል ቼክ መሙላት አያስፈልግም። የሚታዩትን ቁጥሮች ያስገቡ እና የተጠቆመው መጠን ከመለያው ወጪ ይደረጋል።**







ይህ ዘዴ ለወደፊቱ የክፍያ ነባሪ እንዲሆን ከፈለጉ፣ **እንደ ነባሪ ተጠቀም የሚለው ሳጥን** ላይ ምልክት ያድርጉ። በ**እኔ ጋሪ** በኩል ክፍያዎችን ከማስገባትዎ በፊት፣ ሁልጊዜ የመክፈያ ዘዴዎችን የመቀየር አማራጭ አለዎት።

የመክፈያ ዘዴውን ለማስቀመጥ **አስቀምጥ** የሚለውን ጠቅ ያድርጉ። ከፈለጉ ሌላ የክፍያ አማራጭ ማከል ይችላሉ፣ ወይም ወደ ቀደመው ስክሪንዎ ለመመለስ ተመለስ የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።

## አማራጭ ክፍያዎች

አንዳንድ ትምህርት ቤቶች በCampus Parent በኩል የተወሰኑ አማራጭ ክፍያዎችን (እንደ እንቅስቃሴ ማለፊያ፣ የዓመት መጽሔቶች፣ ወዘተ ያሉ) የመክፈል ምርጫ ለወላጆች ይሰጣሉ።

ያሉትን አማራጭ ክፍያዎች ለማየት **ክፍያዎች** የሚለውን ይምረጡ እና በማያ ገጹ ግርጌ አጠገብ ያለውን **አማራጭ ክፍያዎች**ን ጠቅ ያድርጉ።




ማንኛውም የሚገኙ አማራጭ ክፍያዎች ለተመረጡት ተማሪዎች ይታያሉ። በፈለጉት ማንኛውም ክፍያ ላይ **ወደ ጋሪ አክል** የሚለውን ጠቅ ያድርጉ፣ ከዚያም ክፍያ ለመፈጸም **የእኔ ጋሪ**ን ጠቅ ያድርጉ ወይም ወደ ቀድሞው ስክሪን ለመመለስ **ተመለስ** የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።




ስለ ማንኛውም የተመደቡ ወይም አማራጭ ክፍያዎች ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን የተማሪዎን ትምህርት ቤት ያነጋግሩ። በኦንላይን የክፍያ ስርዓት ላይ ቴክኒካዊ ችግር ካጋጠምዎ በ 816-359-5000 ላይ የእገዛ ዴስክን ማነጋገር ይችላሉ።